Global Amhara Coalition

United States of America

1103 Amherst Avenue, Suite 2

Silver Spring, MD 20902

ሰኔ 5 ቀን 2013 ዓ/ም

# ከዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት(Global Amhara Coalition) የተሰጠ የሀዘን መግለጫ

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት(Global Amhara Coalition) በዕውቁ  የስነፅሁፍ ፣ ቋንቋና: ታሪክ ሊቅ  በፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ህልፈተ ህይወት ምክንያት የተሰማውን ጥልቅና መሪር ሀዘን ይገልፃል::

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ወደር ከማይገኝላቸው በጣት ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ውስጥ አንዱ ነበሩ:: ከሰባት አስርተ አመታት በላይ በግዕዝ ቋንቋ ምርምርና ትርጉም ፤ በገዳማትና በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ጥልቅ የሆነ ምርምር በማካሄድ ብዙ መፃህፍትንና የምርምር ፅሁፎችን ለትውልድ አበርክተዋል::
ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ወደር የማይገኝላቸው የታሪክ ሊቅ ብቻ ሳይሆኑ ለሀገራቸው አርበኛም ነበሩ:: ከምርምር ስራቸው ባልተናነሰ  ኢትዮጵያ የተሻለ ስርአተ መንግስት እንዲኖራት በተደረጉት እልህ አስጨራሺ ጥረቶች ሁሉ ከግምባር በመሆን አቅጣጫ በማመላከትና በማስተባበር እስከ ህልፈተ ህይወታቸው ድረስ የላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል::
ፕ/ር ጌታቸው እጅግ ለሚወዷት አገራቸው ኢትዮጵያና ለትውልድ ያስተላለፉት ቅርስ በጣም ጥልቅና በርካታ ነው:: እርሳቸው ከሚጠበቅባቸው በላይ አበርክተው አልፈዋል:: ዋናው ጥያቄ የአሁኑና መጪው ትውልድ ይህንን የእርሳቸውን አደራ ተቀብሎ አርያቸውን ተከትሎ አገርንና ታሪክን በአግባቡ የመጠበቅና ለትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት በብቃት የመወጣት መሆን ይኖርብታል ብሎ ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት በፅኑ ያምናል::
የፕሮፌሰር ጌታቸው እውቅ ስራወቸም በትውልዱ እንዲሰርፁና እንዲዘከሩ ህብረቱ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል:: በተለይ በአሁኑ ወቅት የአገራችን ጥንተ ታሪክ እኩይ በሆኑ የፓለቲካ ኃይሎች  በሀሰት ትርክት እየተበረዘ ባለበት አስጊ ሁኔታ የፕሮፌሰር ጌታቸውና መሰል እውነተኛ ምንጮች በመጠቀም የቀረቡ ስራወች ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ተፈላጊነታቸው የጎላ ነዉ::
ከዚህም የተነሳ ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት የኢትዮጵያም ሆነ የአማራው ታሪክና ስልጣኔ በተገቢው ሁኔታ ትውልድ እንዲያውቀው ፤ እንዲጠብቀውና: ለመጪው ትውልድም ማስተላለፍ እንዲችል የሚያግዝ ስራ መጀመር ብቻ ሳይሆን በተጠናከረ ሁኔታ እንደሚቀጥልበት ቃል ይገባል:: ይህን በማድረግ ፕ/ር ጌታቸው ለትውልዱ ያስተላለፉትን

አደራ ለመወጣት የበኩሉን ድርሻ በመወጣት ምሳሌ ይሆናል::
በእውነት ኢትዮጵያ ትልቅ ሰው ፣ትልቅ ሊቅ አጣች:: ስራወቻቸው ግን ህያው ሆነው በትውልድ ሲዘከሩ ይኖራሉ::
ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት ለፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ቤተሰቦች፣ ጓደኞች፣ የስራ ባልደረቦችና: ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መፅናናትን ይመኛል::

ነፍሳቸውን በአፀደ ገነት ያኑርልን::

ዓለም አቀፍ የአማራ ህብረት (Global Amhara Coalition)